# ይድረስ ለፕሮፌሰር መስፍን፤ “የአንድነት ፓርቲ ማፈሳዊ ሚ”

ክቡር ሆይ! የናፍቆቴን ያህል እንደምን አሉ? እኔ እንዳለሁ አለሁ። እኔና እርስዎ ከተዋወቅን እነሆ አስር ዓመት መሆኑ ነው። ከዚያ በፊት እርስዎ ባያውቁኝም እኔ በዝና አውቅዎት ነበር። በአንድ የእርስዎ “የጡት ልጅ” አማካይነት ከተዋወቅን በኋላ በብዙ ሀገራዊ አጀንዳዎች ዙሪያ ለረጅም ሰዓታት ተወያይተናል። ተከራክረናል። በነዚያ የውይይት ጊዜአት ከእኔ አምነው የተቀበሉት አንድም ነገር እንደሌለ ተገንዝቤአለሁ። በበኩሌ ግን በርካታ ቁም ነገሮችን መቅሰሜን አልሸሽግም። እግረ መንገዴንም የእርስዎን ማንነት በቅርብ ሆኜ እንድገነዘብ እድል አግኝቻለሁ። በውይይታችን ወቅት አንዳንዶቹ ሃሳቦችዎ ተቀባይነት እንደሌላቸው ገፋ አድርጌ ስናገርዎ (ቻሌንጅ ሳደርግዎ) ያሰሙት የነበረውን አባታዊ “ኃይለ ቃል” ዛሬም በጊዜ መርዘም የምዘነጋው አይደለም። በላይ በላዩ ላይ የሚለኩሱትንም ትምባሆ እንዲሁ!

ክቡር ሆይ! ለዓመታት አፎቱ ውስጥ የከተትኩትን ብዕር አንስቼ ይህንን ጦማር እንድከትብልዎ የቀሰቀሰኝ ሰሞኑን ከአንድነት ፓርቲ መውጣትዎን ከዚሁ ጋዜጣ ላይ ማንበቤ ነው። ለዘመናት ከቆዩበት የትግል ሜዳ “በማፈግፈግዎ” የተሰማኝን “ሀዘን” ከመግለጥ ይልቅ፤ በኢትዮጵያ የተቃውሞ ፖለቲካ ትግል ውስጥ ያሳለፉትን “ጀግንነት የተሞላበት ገድል” አርባና ሃምሳ ዓመታት ወደኋላ በመመለስ አጭር ዳሰሳ ማድረግን መረጥኩ።

መላው ዓለም እንደሚገነዘበው፤ ክቡርነትዎ በስልጣን ላይ ያለን መንግስት “መጎነጥ” ይወዳሉ። በወጣትነት ዘመንዎ የንጉስ ኃይለ ስላሴን ‘አልጋ’ አንቀጥቅጠዋል። ታዲያ ምን ያደርጋል፣ ትግሉ ሲፋፋምና ሲጋጋል ወደኋላ ቀረት አሉና (መቼም ስልጣን አይወዱም አይደል?!) በዘመኑ የነበሩ የመሬት ላራሹ አቀንቃኝ ወጣቶች ፊት ፊት እንዲሄዱ ዕድል ሰጧቸው። ብዙዎቹ ጉብሎች መታሰር፣ መገረፍ፣ መጋዝና መንገላታት ሲገጥማቸው እርስዎ “ወደፊት ለመሄድ ወደኋላ አፈግፍግ” በሚለው ያልተጻፈ መመሪያዎ ከኋላ ሆነው “ግፋ በለው” የሚለውን ስልት ይከተሉ እንደነበር ዛሬ ዕድሜ ያጎበጣቸው የትውልድዎ ሰዎች አጫውተውኛል። በዚያ ዘመን ላደረጉት “ጊዜ የማይሽረው ትግል”ም በወለጋ ክፍለ ሀገር የወረዳ ገዥ ሆነው በንጉሱ መሾምዎን ሰምቻለሁ።

የአፄ ኃይለ ስላሴ ዘውዳዊ አገዛዝ በዚህ መልኩ በተደረገ መጠነ ሰፊና እልህ አስጨራሽ ትግል አክትሞ የደርግ ስርዓት መንበረ ስልጣኑን ሲጨብጥ፤ አገረ ገዥ ሆነው ያገለገሉት የፊውዳል ስርዓት በሀገርና በሕዝብ ላይ ያደረሰውን በደልና ጭቆና ለማጋለጥ “መርማሪ ኮምሲዮን” ሲቋቋም የአብዮቱ ግንባር ቀደም ተዋናይ ሆኑ። የማጣራቱ ሂደት አለመፍጠን ያሳሰበው ደርግ “ምነው?” ሲልዎት ደግሞ ጀግንነት በተሞላበት አኳኋን “ጠመንጃው እኮ በእጃችሁ ነው!” የሚል ምላሽ በመስጠትና ከአብዮቱ ጎን በመሰለፍ ለፍትህና ለርትዕ ያለዎትን ቁርጠኛ አቋም አረጋገጡ።

ይሁን እንጂ፣ ደርግ በአፄው መንግስት ዋና ዋና ባለስልጣናት ላይ ያነሳውን ጠመንዣ በርዝራገሮቹ ላይ ላለማነሳቱ ዋስትና እንደሌለ ሲገነዘቡ፤ “ወደፊት ለመሄድ ወደኋላ አፈግፍግ” በሚለው ስልትዎ መሰረት በዩኒቨርሲቲው ቅጥር ግቢ

መሸጉ። ምሁራዊ ስትራቴጂ በመንደፍ ፋሽሽታዊውን ደርግ ድምፅዎን አጥፍተው ያርበደብዱት እንደነበር ታሪክ የመዘገበው ሀቅ ነው። ይህም የትግል ስልት ደርግን እንዳሽመደመደው ሲገነዘቡ፣ ከነበሩበት የምሁራን አጸድ በመውጣት “ደርግ እንግዲህ በቃህ! የሽምግልና መንግስት ይቋቋም” የሚል ሃሳብ ከማቅረብ አልፈው፤ በትጥቅ ትግል ወደ አዲስ አበባ በመገስገስ ላይ የነበሩትን “ወያኔዎች” ለንደን ድረስ በመሄድ ኢሳይያስ አፈወርቂንና መለስ ዜናዊን ማነጋገርዎን ከእርስዎ ጋር አብረው ሄደው የነበሩ ሰው በአንድ ወቅት አጫውተውኛል። “ኢሳይያስ ከአቶ መለስ የተሻሉና ሀገር የመምራት ብቃት ያላቸው” (Charismatic Leader) መሆናቸውንም ለእኒሁ አብሮውዎት ለሄዱት ሰው “ሹክ” ማለትዎን ሰውየው ጨምረው ነግረውኛል።

የሽምግልና መንግስት የማቋቋሙ ነገር “ወያኔ በጫካ ሕግ የሚመራ፣ ጠመንጃ ነካሽ” በመሆኑ፤ ደርግም “የፖለቲካ ጉዳይ የባልና ሚስት ጠብ” እንዳልሆነ በመግለጽ ግታራ አቋም በመያዛቸው ሊሳካ አልቻለም። ነገሩ ሁሉ ተፋጠነና ደርግ ወድቆ “ወያኔ” ስልጣን ያዘ። የኢትዮጵያን ሕዝብ የዴሞክራሲ ስርዓት ተጠቃሚ ለማድረግ የነበረዎት ህልምና ይህንንም ህልም እውን ለማድረግ የሚያደርጉት “ትግል” መቆም ስለሌለበት እንደተለመደው “ወደፊት ለመሄድ ወደኋላ በማፈግፈግ” ምሁራዊ ጥበብዎ በመጠቀም ለሌላ ትግል ቆርጠው ተነሱ።

ለዚህ ወቅት የሚመጥነው የትግል ስልት ሰላማዊ መሆን እንዳለበት ለመወሰን ጊዜ አላባከኑም። በዚህም መሰረት ከ“ወያኔው” መሪ ከአቶ መለስ ዜናዊ ጋር በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን አማካይነት ሰፊ ክርክር በማድረግ “አማራ” የሚባል ብሔርና ሕዝብ የሌለ መሆኑን (በቅርብ ጊዜ ግን ይህንን ሃሳብ አንስተዋል) በማረጋገጥ የወያኔን “የጎሳ ፖለቲካ” አፈር-ድቤ አስጋጡት።

ከ“ወያኔ” ጋር የሚደረገው ግብ ግብ በዚህ መልኩ ተጀመረ። በወቅቱ ሁሉም በየመንደሩ እየተቧደነ በወያኔ ላይ “ወፈ-ሰማይ” ተቃዋሚ ፓርቲ በመነሳቱና እርስዎ ደግሞ “በጎሳ” ተደራጅቶ መታገልን ስለማያምኑበትና እነ ፕሮፌሰር አስራት “ለሌለ ብሄርና ለሌለ ሕዝብ” መዐሕድን ማቋቋማቸው “ጠባብነት” መሆኑን ቀድመው ስለተገነዘቡ (ሀገራዊ አደረጃጀት ያለው ፓርቲ እስከሚመሰረት ደረስ ትግሉ እንዳይቆም) የወያኔን መንግስት የሚያጋልጥ የሰብአዊ መብት ተሟጋች ድርጅት በማቋቋም በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ በየወቅቱ በተነሱ “ገዥዎች” ላይ የሚያደርጉትን ትግል ቀጠሉ።

ከዓመታት በኋላ ብቅ ብቅ ያሉ ሕብረ ብሔራዊ አደረጃጀት ያላቸው ፓርቲ መሪዎችንም “አይዞአችሁ፣ በርቱ” ከማለት ባሻገር አንዳንድ የኢሰመጉ አባላትን በመላክ አመራራቸውን እንዲያጠናክሩ ያደረጉት ጥረት ምንጊዜም የኢትዮጵያ “የቁርጥ ቀን ልጅ” መሆንዎን ያረጋግጣል። ይሁን እንጂ፣ እነዚያ ፓርቲዎች በክቡርነትዎ የሚሰጣቸውን “መንፈሳዊ ምክር” በመቀበል ወደፊት እንደመግፋት እርስ በራሳቸው በመሻኮት የሚያጠፉት ጊዜ በመብዛቱና ይህም የወያኔን ዕድሜ የሚያረዝመው በመሆኑ ችግሩን በሽምግልና ለመፍታት ስልት ቀየሱ። ከወዳጆችዎ ጋር ሆነው ብዙ ጥረት አደረጉ። ግን አልተሳካም። እናም የራስዎን ፓርቲ በማቋቋም እነዚያን እልህ የተጋቡ የፓርቲ መሪዎች በማቀራረብ የማዋሃድ ስትራቴጂ ቀየሱ። ተሳክቶልዎት “ቅንጅት”ን መመስረት ቻሉ።

ከአርባ ዓመታት በላይ ብዙ ውጣ ውረድ ያዩበትን ህልም "ቅንጅት" እውን እንደሚያደርግ አልተጠራጠሩም። እርስዎም በአባልነት ያሉበት ከአራቱ ፓርቲዎች የተውጣጣ ኮሚቴ ስራውን እንደጀመረ በአመራሩ መካከል ያለውን "ጥላቻ ለማጥፋትና ደመኛነትን ለማስወገድ" ወደ ቢሾፍቱ በመውሰድ የዕርቅ መድረክ ፈጠሩ። ሽኩቻው ግን ሊቆም አልቻለም። እንዲያውም በዕጩ ምልመላ ወቅት በተፈጠረው መሳሳብ ምክንያት "ቅንጅት" ወደ መፍረስ ተቃርቦ ነበር። በ"ቅንጅት" ዙሪያ የተሰባሰበው ኃይል በርካታ ጊዜውን የሚያጠፋው በንትርክና በጭቅጭቅ መሆኑን ሲያዩና ይህ ኃይል አንድ ሆኖ በመስራት ውጤት ላይ እንደማይደርስ ሲገባዎት ደግሞ፣ "ወደፊት ለመሄድ ወደኋላ አፈግፍግ" በሚለው ስልትዎ በመጠቀም (ትግሉን ከፊት ለፊት ሆኖ ችግሮቹን እየፈቱ እንደመምራት) ከኋላ ሆነው "ግፉ በለው" ማለትን መረጡ።

በዚያ ወቅት ከ"ቅንጅት" ለመውጣት በጻፉት ማመልከቻ ያቀረቡት ምክንያትም "ቅንጅት የቅቤ ገበያ ሆኗል። እኔ በዚህ አካል ውስጥ ሆኜ የታሪክ ተጠያቂ መሆን አልሻም" የሚል እንደነበር ይታወሳል። የሚገርመው ነገር እርስዎ ሊኖሩበት ያልፈለጉትን "ቅንጅት" ሌሎች "በቅቤ ገበያው ውስጥ መሆን አንፈልግም" ብለው መልቀቂያ ሲያቀርቡ እርስዎ ጭምር ያወረዱት ውግዘት ነው። ማን በታሪክ ተጠያቂ መሆንን ይመርጣል?

እርስዎ ከ"ቅንጅት" አመራር ራስዎን ቢያገሉም፣ "ቅንጅት" ከቅቤ ገበያነት ባሻገር ጠንካራ ተቀናቃኝ ሆኖ ምርጫውን አጠናቀቀ። ከዚያ በኋላ እርስዎም የ"ቅንጅት መንፈሳዊ መሪ" (እንደ ሃማሱ ሼህ አህመድ ያሲን) በመሆን በየሳምንቱ መግለጫ በመጻፍ ትግሉን በአሸናፊነት ለመደምደም ብርቱ ጥረት አደረጉ። "ቅንጅት" በውህደት ወደ ፓርቲነት ሲሸጋገር ከአራቱ ፓርቲዎ ተመርጠው የሚመጡ አመራር አባላት እነማ በሆን እንዳለባቸው ዕቅድ ነድፈው ከአስፈጻሚዎ ከዶ/ር ብርሃኑ ጋር በመሆን የስም ዝርዝራቸውን "የሚደገፉ" እና "የማይደገፉ" በማለት በየፓርቲዎቹ ውስጥ ላሉ ታማኝ ሰዎቻችሁ ላካችሁ። (ይህንን ሁኔታ በተመለከተ ዶ/ር ብርሃኑ በመጽሐፉ ውስጥ አንድ ድብቅ ኮሚቴ ተቋቁሞ የውህደቱን ስራ ከመጋረጃው በስተጀርባ ሆኖ ያከናውን እንደነበር ገልጿል)

ይህንን ሽፍጥ የተገነዘቡ የአንዳንድ ፓርቲ መሪዎች በውህደቱ ላይ ሲያንገራግሩ ክቡርነትዎ ቤትዎ ድረስ በመጥራት "እከሌ እንዲህ ካላደረገ በጋዜጦች ላይ እንዲህ ብየ እጽፍበታለሁ" በማለት ጭምር (በተለይ ወጣት ፖለቲከኞችን) ለማሸማቀቅ ያደረጉት ጥረት ዛሬም ያልዘነጋሁት ሀቅ ነው። በዚህ መልኩ "ቅንጅት" በግድ እንዲዋሃድ ተደረገ። "የቅቤ ገበያ ነው" ብለው ትንቢት የተናገሩለት "ቅንጅት"ም (በሽፍጥ በመቋቋሙ ምክንያት) ረጅም ርቀት ሳይሄድ አደጋ ተደቀነበት። ሁሉም ነገር በአጭር ጊዜ እንዳልነበር ሆነ። አበው "ደባ ራሱን ስለት ድጉሱን" እንዲሉ፣ እርስዎም በመጠሪያ ዘመንዎ በአሳዛኝ መልኩ እስር ቤት ወረዱ። ከብዙ መንገላታት በኋላ፣ "ለደረሰው የንብረት ውድመትም ሆነ የሕይወት መጥፋት ተጠያቂ መሆንዎን" አምነው፣ መንግስትን ይቅርታ ጠይቀው "በጀግንነት" ተፈቱ።

ከዚያ በኋላ ፊትዎን ወደ ፖለቲካ አያዞሩም ብለን ስንጠብቅ፣ በሕንድ አገር በህክምና ላይ ሆነው "ዝራፍ" ማለትዎን የአሜሪካ ድምፅ ሬዲዮ አበሰረን። በዚያው ቃለ ምልልስዎ "በብርቱካን አመራር የቅንጅት ትግል ወደ ከፍተኛ ደረጃ እንደሚሸጋገር" ትንቢት ነገሩን። የ"ወያኔ" መንግስት "ቅንጅት" የሚለውን ስም

ባይሰጥም የእርሱ “ወራሽ” የሆነውን “አንድነት” በትንቢቱ መሰረት አቋቋሙ። ከፍተኛ አመራር ሆነውም ተመረጡ። “አንድነት” በአጭር ጊዜ 100 ጽ/ቤቶችን ከፍቶ የኢትዮጵያን ሕዝብ ከ”ወያኔ” አገዛዝ ነፃ ሳያወጣ፣ ሰሞኑን “የመፈረካከስ” አደጋ እየደረሰበት መሆኑን ጋዜጦች እየነገሩን ነው። ክቡርነትዎም “አንድነት ፓርቲ በአራት ወር ዕድሜው መሰነጣጠቅ እየታየበት ነው። …በዚህ ከቀጠለ ደግሞ የኢትዮጵያን ሕዝብ ዳግም ተስፋ ማስቆረጥ ላይ ስለሚያደርስ ይህንን የታሪክ ስህተት ውስጡ ሆኜ ከምመለከት ራሴን ከደሙ ንፁህ ለማድረግ ከዛሬ ጀምሮ እገደዳለሁ” የሚል ሃሳብ የያዘ ማመልከቻ ጽፈው ከአንድነት ፓርቲ መልቀቅዎንም እነዚሁ ጋዜጦች እየጻፉ ነው። ትግሉ መሰናክል ከገጠመው በተለመደው “ወደፊት ለመሄድ ወደኋላ አፈግፍግ” በሚል ስልት ጥግ መያዝ ነው እንጂ ማን በታሪክ ተጠያቂ ሊሆን?

ክቡር ሆይ! ይህንን ሁሉ የረጅም ዘመን “ትግልዎን” በዚህ ጽሁፍ ለማውሳት የፈለግኩት ያለምክንያት አይደለም፡፡ እንደ ወቅቱ ሁኔታ ወደፊትም እየቀደሙ ትንቢት በመናገር እንዲሁም ወደኋላ እያፈገፈጉ ያደረጉትን “መራራ ትግል”ና ለኢትዮጵያ ሕዝብ ያደረጉትን መልካም ውለታ አንዳንድ ወገኖች ባለመረዳታቸው ወይም ሆን ብለው በማጣመም እጅ ሰባራ እንዳያደርጉዎት በማሰብ ሀቁ በታሪክ መዝገብ ላይ እንዲሰፍር በማሰብ ነው ይህንን መጣጥፍ ለመጫር የተነሳሁት።

ከአንድነት ፓርቲ አመራር ለመልቀቅ ማመልከቻ ማቅረብዎን የሰሙ አንዳንድ የዋሆች ነገሩን አቅልለው በማየት አሉታዊ ትርጉም ቢሰጡት እንኳ፣ እርስዎን ሊያሳስብዎት አይገባም። ዱሮም እኮ “ሲፋጅ በማንኪያ ሲበርድ በእጅ” ነው ተረቱ። ሁሉም ነገር በትክክለኛው መስመር መሄድ ሲችልና ትግሉ እንከን ካልገጠመው፣ ፊት ለፊት በመውጣት ሕዝቡን “አለሁልህ” ማለት ነው እንጂ ለትግሉ እንቅፋት የሆኑ የጎንዮሽ ትግሎችን መጋፈጥ ለእርስዎ የሚመጥን አይደለም። ለዘመናት የተመዘገበው የትግል ታሪክዎም ቢሆን፤ ጭንቅና ችግር ሲገጥም መጋፈጥን ሳይሆን ወደ ኋላ ማፈግፈግን የሚያሳይ በመሆኑ በዚህ ወቅት አዲስ የአሰራር ስርዓት ሊዘረጉ እንደማይገባ ወዳጅም ሆነ ጠላት ሊገነዘብልዎ ይገባል።

አንዳንድ ወገኖች በዚህ ዕድሜዎ ለሀገርዎ የሚያደርጉትን መጠነ ሰፊ ትግል ከምንም ባለመቁጠር “ምናለ አሁን ፖለቲካው ቢቀርባቸው?” ሲሉ ይደመጣሉ። ይህንንም አይስሙ። “ስልጣን በቃኝ” ብሎ ከፖለቲካ ራሱን ጡረታ ያወጣው የትኛው ኢትዮጵያዊ ነው? አፄ ኃ/ስላሴ እንኳ እስከ 84ኛ ዓመታቸው ድረስ ሀገራቸውን አገልግለዋል አይደል? ታዲያ እርስዎ ራስዎን ከፖለቲካ ጡረታ አውጥተው ለትውልድ መጥፎ አርአያ መሆን ይገባዎታል? ደግሞስ “እነርስዎ” ከሌላችሁ ትግሉ ምን ይውጠዋል? እነልደቱን አምናችሁ አትተውት ነገር አስቸጋሪ ነው፡፡ ደግሞም እናንተን አምነን ከእነርሱም ጋር ተቀያይመናል። እናም፣ ችግሩ ብዙ ነው።

ክቡር ሆይ! ከዚህ በላይ ብዙ በመጻፍ የትግል ጊዜዎትን ማባከን አልሻም። መቼም ክንድዎን አልተንተራሱምና ለዚህ ጦማሬ መልስ መስደድዎ ስለማይቀር ቀሪውን ታሪክዎን ከመልሱ መልስ ጋር አባሪ አድርጌ እንደማቀርብ ቃል በመግባት ለዛሬው እሰናበትዎታለሁ።

**ምንጊዜም አክባሪዎ፤ ፍቅሩ አየለ በላይ**